ONE VOICE
FELLOWSHIP

# Worship Service

**February 28, 2021**

## Prelude | Welcoming One Another

*English*

**I love you with the love of the Lord**

I love you with the love of the Lord
Yes, I love you with the love of the Lord
I can see in you the glory of my King
Yes, I love you with the love of the Lord

**Jesus, I lift Your Name Higher**

**Chorus:**
Jesus, I lift your name higher
  I lift Your name higher (ALL)
Jesus, I lift your name higher
  I lift Your name higher (ALL)
Jesus, I lift your name higher
  I lift Your name higher (ALL)
For you're worthy of my praise
Jesus, I lift Your name higher

When I look back through the years
There is nothing I can compare
To the grace and mercy I've been shown
Except to sing of your greatness
You are my Redeemer, my all in all,

Chorus (x2)

I lift your name higher

## Song of Praise | Psalm 27

*English*

Of this I am sure
I will see God's goodness
My soul will rest in
the land of the living
Be strong in the Lord

**Chorus:**
The Lord is my light
And my salvation
Whom shall I fear?
Shall I be afraid?
The Lord is my life

One thing I need
One thing I ask you
To dwell in your house
Each day of my life
Delighting in you

Chorus (x2)

In trouble time
He keeps me secure
He covers me
He lights my head
Above the storm

## Call to Worship | Psalm 27

**Jorge & Sonia** | *Spanish & English*

**መዝሙር 27: 1-14**

1 እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኅኔ ነው፤
የሚያስፈራኝ ማን ነው?C
እግዚአብሔር ለሕይወቴ ዐምባዋ ነው፤
ማንን እፈራለሁ?

**1 The Lord is my light and my salvation; whom shall I fear?**
**All: The Lord is the stronghold of my life; of whom shall I be afraid?**

4 እግዚአብሔርን አንዲት ነገር እለምነዋለሁ፤
እርሷንም እሻለሁ፤
ይኸውም በሕይወቴ ዘመን ሁሉ፣
በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፣
የእግዚአብሔርን ክብር ውበት አይ ዘንድ፣
በመቅደሱም ሆኜ አሰላስል ዘንድ ነው።

4 One thing have I asked of the Lord, that will I seek after:

**that I may dwell in the house of the Lord all the days of my life, to gaze upon the beauty of the Lord and to inquire in his temple.**

10 አባቴና እናቴ ቢተዉኝ እንኳ፣
እግዚአብሔር ይቀበለኛል።

10 Though my father and my mother have forsaken me, but the Lord will take me in.

11 እግዚአብሔር ሆይ፤ መንገድህን አስተምረኝ፤
ስለ ጠላቶቼም፣
በቀና መንገድ ምራኝ።

**11 Teach me your way, O Lord, and lead me on a level path because of my enemies.**

12 ለጠላቶቼ ፍላጎት አሳልፈህ አትስጠኝ፤
የሐሰት ምስክሮች ተነሥተውብኛልና፣
ዐመፃ የሚረጩ ናቸው።

12 Give me not up to the will of my adversaries; for false witnesses have risen against me, and they breathe out violence.

13 የእግዚአብሔርን ቸርነት፣
በሕያዋን ምድር እንደማይ፣
ሙሉ እምነቴ ነው።

**13 I believe that I shall look upon the goodness of the Lord in the land of the living!**

14 እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፤
አይዞህ፣ በርታ፤
እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።

14 (*English*): Wait for the Lord; be strong, and let your heart take courage; wait for the Lord!

## Opening Prayer

**Clément** | *Swahili & English*

## Scripture Reading | Ephesians 1:3-14

**Mike** | *Arabic*

**ኤፌሶን 1: 3-14**

3 በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ የባረከን የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤

4 በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ
በእርሱ መርጦናልና። በፍቅር፣

5 በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ፣ እንደ በጎ ፈቃዱ አስቀድሞ
ወሰነን፤

6 ይኸውም፣ በሚወደው በእርሱ በኩል በነጻ የተሰጠን ክቡር የሆነው
ጸጋው እንዲመሰገን ነው።

7 በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ባለጠግነት መጠን፣ በደሙ በተደረገ
ቤዛነት፣ የኀጢአትን ይቅርታ አገኘን፤

8 ጸጋውንም በጥበብና በማስተዋል ሁሉ አበዛልን።

9 በክርስቶስ ያቀደውንም የፈቃዱን ምስጢር እንደ በጎ ሐሳቡ እንድናውቅ
አደረገ።

10 በዘመን ፍጻሜ ይሆን ዘንድ ያለው ሐሳቡ በሰማይም በምድርም
ያሉትን ነገሮች ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሥር ለመጠቅለል ነው።

11 ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ
አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል፤

12 ይኸውም በክርስቶስ ተስፋ በማድረግ የመጀመሪያ የሆንነው እኛ
ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው።

13 እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይህም የድነታችሁን ወንጌል በሰማችሁ
ጊዜ ወደ ክርስቶስ ተጨምራችኋል፤ አምናችሁም፣ በእርሱ በመሆን ተስፋ
ሆኖ በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ታትማችኋል።

14 ለክብሩ ምስጋና ለመሆን የእግዚአብሔር የሆኑት እስኪዋጁ ድረስ፣
እርሱ ለርስታችን ዋስትና የሚሆን መያዣ ነው።

## Song of Praise | Jalali Yesu

*Urdu*

You are full of grace and truth (men)
You are full of grace and truth (women)
Jalali Yesu (men)
Jalali Yesu (women)

**Chorus:**
Jalali Yesu (men)
Jalali Yesu (women)

You are great and you are good (men)
You are great and you are good (women)
Jalali Yesu (men)
Jalali Yesu (women)

Chorus (x4)

You are glorious
Over all the earth (3x)
You are glorio-o-o-us!

You are making all things new (men)
You are making all things new (women)
Jalali Yesu (men)
Jalali Yesu (women)

## Tithes & Offerings

**Jorge & Abrham**

Give online at:

- ChurchCenter mobile app
- onevoicefellowship.org/give

## Praying Together as a Family

**Yaovi** | *In our own languages*

## Sermon

**Chris Sicks** | *English*

የስብከቱ ቅጅ በገጽ 4 ላይ በቋንቋዎ ይሆናል

## Respond in Song | Jesus, I lift Your Name Higher

*Many Languages*

**Chorus:**
Jesus, I lift your name higher
I lift Your name higher (ALL)
Jesus, I lift your name higher
I lift Your name higher (ALL)
Jesus, I lift your name higher
I lift Your name higher (ALL)
For you're worthy of my praise
Jesus, I lift Your name higher

When I look back through the years
There is nothing I can compare
To the grace and mercy I've been shown
Except to sing of your greatness
You are my Redeemer, my all in all,

Chorus (x2)

I lift your name higher

## Communion

**Chris Sicks** | *English*

**Who can participate in the Lord's Supper?**

The Lord's Supper is a sacrament—a holy interaction between God and His people. It celebrates the spiritual union that Christians have with Christ. It is also called communion, because it strengthens the community we share with every brother and sister who trust in Jesus alone for salvation.

God's Word warns us that "Whoever eats the bread or drinks the cup of the Lord in an unworthy manner will be guilty concerning the body and blood of the Lord." (1 Corinthians 11:27) We must think carefully about this sacrament. It is only for those who:

1. have examined their conscience,
2. who truly understand the nature of the body of Christ,
3. who have committed their entire life to following Him,
4. who are members of a bible-believing church.

Before you come to the table you must first come to Jesus in faith!

We are not to judge people's hearts. Ask the Holy Spirit to examine your heart. If you are not sure about your relationship with Christ, do not participate in the sacrament. Instead, please let us pray for you. We love you and want you to join our community! But first you must be joined to Christ. Our leaders are available to talk and pray with you, to help you on your journey.

*"If you confess with your mouth that Jesus is Lord and believe in your heart that God raised him from the dead, you will be saved. For with the heart one believes and is justified, and with the mouth one confesses and is saved."* (Romans 8:9-10)

## Prayer of Thanks

**Mamatili** | *Uyghur*

## We Respond, Rejoice, and Reach
*Our promise as a church*

**Chris Sicks** | *English*

**ALL:**
By the power of the Holy Spirit,
we live in harmony with our brothers and sisters in Christ's Body.
We worship and glorify God the Father together with one voice.
And we welcome our neighbors as Christ welcomed us, for the glory of God.

## Benediction

**Chris Sicks** | *English*

# መልዕክት:
# ለኃይል መፀለይ

የሚቀርብ መልዕክት: 2021 ፌብሩወሪ 28, እሑድ

መጋቢ ክሪስ ሲክስ

## መግቢያ

በሐምሌ ወር ሣምንታዊ አምልኰን ለመጀመር በምንዘጋጅበት ጊዜ ትንሹን ማህበረሰብ እንደቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ እየገነባን ነዉ። በኤፌሶን መጽሐፍ ላይ ጊዜ እየወሰድን ነበር። ምክያቱም እዚህ ላይ ስለቤተ ክርስቲያን ተፈጥሮና እግዚአብሔር እንዴት እርስ በርሳችን መዋደድ እንደሚገባን፣ እርሱንም እንዴት ማክበር እንደሚገባን ብዙ የሚለዉ ነገር አለ።

ዛሬ ኤፌ. 3፡14-21 ን እንመለከታለን። ጥቅሶቹን በእንግሊዘኛ አንብቤ እፀልያለሁ። በልብህ ቋንቋ የመልዕክቱ ቅጅ ካለህ ሲነበብ እያደመጥከኝ እባክህ እግዚአብሔር በባረከህ ዉብ ቋንቋ ጥቅሱን አንብብ።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንባብ

**ኤፌሶን 3: 14-21**

14-15 ስለዚህ ምክያት በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ

16-17 በመንፈሱ በዉስጥ ሰዉነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደክብሩ ባለጠግነት መጠን ይስጣችሁ፣ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ

18-19 ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታዉም፣ ጥልቀቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፣ ከመታወቅም የሚያልፈዉን የክርስስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፣ እስከ እግዚአብሔርም ፍፁም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ።

20 እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራዉ ኃይል መጠን ከምንለምነዉ ወይም ከምናስበዉ ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለዉ

21 ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትዉልዶች ሁሉ ከዘላለም ክብር ይሁን፣ አሜን።

## አስተዋፅዖ

1. **አባትህ ሊባርክህ ይፈልጋል**
2. **አባታችን ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ይባርካል**
3. **ኃይል 3 - ለምን እንፀልያለን**

ለጓደኞቻችን ይህንን መልዕክት በተለያየ ቋንቋ ማንበቡን አስታዉስ፡ ያልምንም ብዥታ መከታተል ይቻል ዘንድ መጋቢዉ አንድ ጥቅስ በአንድ ጊዜ እያደረገ ያነባል። የጥቅሶቹ ቁጥር እያደመጥህ እንድትከታተል ይረዱሃል።

## 1. አባትህ ሊባርክህ ይፈልጋል

### 14 በዚህ ምክኒያት በአብ ፊት በጉልበቶቼ እንበረከካለሁ

ጳዉሎስ በኤፌሶን ላለችዉ ቤተ ክርስቲያን ይፀልያል። ከሙሉ ልቡ ይፀልያል። በፀሎት ተንበርክኮ እንዳለም ይሰማናል። ከ2000 ሺህ ዓመታት በፊት ይሄ የተለመደ የፀሎት አቀራረብ ዘዴ አልነበረም። አብዛኛዉን ጊዜ የአይሁድ ሰዎች በሚፀልዩበት ጊዜ ቆመዉ ነዉ። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ነገሮች በጥልቀት ሲሰማቸዉ፣ እግዚአብሔር ፀሎታቸዉን እንዲመልስ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ለዚህም ሁለት ምክኒያቶች ይቀርባሉ፡

**ዕዝራ 9: 5-6**

5 በሠርክም መሥዋዕት ጊዜ ልብሴና መጎናፀፊያየ እንደተቀደደ ሆኖ ከመዋረዴ ተነሳሁ በጉልበቴ ተንበርክኬ ወደአምላኬ ወደእግዚአብሔር እጄን ዘረጋሁ።

6 እንዲህም አልሁ አምላኬ ሆይ፣ ኃጢአታችን በራሳችን ላይ በዝቷልና በደላችንም ወደሰማይ ከፍ ከፍ ብሏልና አምላኬ ሆይ ፊቴን ወደ አንተ አነሳ ዘንድ አፍራለሁ፣ እፈራማለሁ።

**ሉቃስ 22: 41-44**

41 ከእነርሱም የድንጋይ ዉርወራ የሚያህል ራቀ፣ ተንበርክኮም አባት ሆይ

42 ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ዉሰድ፣ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይፀልይ ነበር።

43 ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታ መልዐክ ታየዉ።

44 በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይፀልይ ነበር፣ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደደም ነጠብጣብ ነበር።

በኤፌሶን 3፡14 ጳዉሎስ በሙሉ ልቡ፣ በጉልበቱ ተንበርክኮ እንደሚፀልይ ይነግረናል። የፀሎቱ ሸክም በኤፌሶን ምዕ. 1-3 ላይ ከጻፈዉ ማንኛዉም ነገር የተነሳ ነዉ። እግዚአብሔር እንደጠራን፣ እንደተቀበለን፣ ኃጢአታችንን

ይቅር እንዳለና እንዳዳነን ያስታዉሰናል። የአንድን ባሕል ወይም ቋንቋ ሕዝብ ብቻ አላዳነም። ነገር ግን እንደእናንተ ያሉትን ሕዝብ ሁሉ ነዉ! ጥሩ ሰዎች ብቻ አላዳነም። ነገር ግን እንደእኛ ያሉትን ኃጢአተኛ ሰዎች ነዉ። ከመንፈሳዊ ሞት አንስቶናል፣ ከክርስቶስ ጋር በመንፈስ በሰማይ አስቀምጦናል። ጳዉሎስ በእግዚአብሔር ኃይልና መልካምት በጣም ከመደነቁ የተነሳ ወደአባቱ በጉልበቱ ተንበርክኮ ነዉ የፀለየዉ።

### 15 በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ዉስጥ ኢየሱስ በሚጸልይበት ጊዜ ወደአባቱ እንደፀለየ እናነባለን። ነገር ግን በክፍለ ጊዜያችን ላይ ቀድመን እንዳደረግነዉ ወደአባታችን ደግሞ እንድንፀልይ አስተምሮናል።

በዓለም ዙሪያ ባሉት በርካታ ባህሎች ልጆች ስማቸዉን የሚያገኙት በምድር ላይ ካሉት አባቶቻቸዉ ነዉ። ስም አንድ ሰዉ ከየትኛዉ ቤተሰብ ጋር እንዳለ ይነግረናል። እያንዳንዱ ቤተሰብ ባሉት የተለያዩ ስሞች ተለይተዉ ይታወቃሉ። እኛን በመመልከት ብቻ መናገር ትችላላችሁ ልክ አይደለም? ሁሉም በዚህ የምናያቸዉ የተለያዩ ዉብ የቆዳና የፀጉር ከለሮች ናቸዉ።

ነገር ግን በቁጥር 15 ላይ ጳዉሎስ አንድ ሰማያዊ አባት እንዳለ ያስታዉሰናል። እርሱም እንደልጁ ስም ሊያወጣልን ባለመብት ነዉ። ክርስቲያን የሚለዉን አንዱን ስም እንጋራለን። ክርስቲያንማለት የክርስቶስ ተከታይ ማለት ነዉ። ኢየሱስ የእኛ ታላቅ ወንድም ነዉ። እግዚአብሔርም የሁላችን አባት ነዉ። አንድ ስምና አባት ከመጋራታችን የተነሳ ቤተሰብ ነን። የእኛ ወንድም የሆነዉ ጳዉሎስ በኤፌሶን ላለችዉ ቤተ ክርስቲያንና ለእኛ ፀልዮልናል ...........

### 16ሀ እንደክብሩ ባለጠግነት መጠን ይስጣችሁ ....

ልግስና ስጦታ ነዉ። ብድር አይደለም። ልግስና ከሞላዉ ሰዉ ጥቂት ብቻ ላለዉ የሚበረከት ስጦታ ነዉ። ሴቷ ልጄ ሉሲ ኮሌጅ እያለች ገንዘብ በምትፈልግበት ጊዜ በስልክ ጠርታኝ አባቴ ሃምሳ ዶላር ያስፈልገኛል ብላ መጠየቁን ታዉቅበታለች። እንምሰጣትም ትረዳለች። ምክኒያቱም ሃምሳ ዶላር እንዳለኝና በትክክለኛ ቦታ ከማዋል አንፃር እምነቴን እንደምጥልባት ይገባታል።

ነገር ግን ሉሲ በስልክ ጠርታኝ አባቴ 50 ሺህ ዶላር እፈልጋለሁ ብትለኝ የለም እንደምላት ታዉቃለች። ምክኒያቱም 50 ሺህ ዶላር የለኝምና! ነገር ግን እግዚአብሔር ለልጆቹ በልግስና ይሰጣል፡በዚህ ቦታ ስለገንዘብ አይደለም እየተናገርሁ ያለሁት። እግዚአብሔር ባለጠጋ ሊያደርጋችሁ ቃል አይገባም። እርሱ ቤተሰባችሁን መመገብ የሚያስችላችሁ፣ በመኪናችሁ ዉስጥ ጋዝ ለመሙላት፣ ኪራይ ለመክፈል የሚያስችላችሁ በቂ ገንዘብ እንዲኖራችሁ ይፈልጋል። ነገር ግን ጳዉሎስ ከገንዘብ ጋር ላልተገናኘ በረከት ይፀልያል፡አሁን ደግሞ ሁለተኛዉን ነጥብ እንመለከት።

## ፪. አባታችን ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ይባርካል


### 16ለ በመንፈሱ በዉስጥ ሰዉነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ እንደክብሩ ባለጠግነት መጠን ይሰጣችሁ ዘንድ

ጳዉሎስ እግዚአብሔር አብ ለቤተ ክርስቲያን የልግስና ስጦታ እንዲያበረክት ይጠይቃል። ያም ትልቅ በረከት ነዉ። ጳዉሎስ እግዚአብሔርን በኤፌሶን ያሉ ወንድሞችና እህቶች በታላላቅ መንገዶች እንዲባርካቸዉ ይለምናል። ይኸዉም እነርሱ በትክክል በሚፈልጉት መንገድ ነዉ። ጳዉሎስ በኤፌሶን ያሉት ክርስቲያኖች ያላቸዉን ተግዳሮት ይረዳል። እነርሱም እኛ ካሉን ተግዳሮት ጋር የሚመሳሰሉ ናቸዉ።

በኤፌሶን ያሉ ክርስቲያኖች ጣዖት በሚመለክበት ከተማ ይኖራሉ። ከተማዋም ሰዎች ኢየሱስ ብቸኛዉ መንገድ፣ እዉነትና ሕይወት መሆኑን እንዲናገሩ የማይፈለግበት ከተማ ነዉ። ያ ዉጫዊ ተግዳሮት ነዉ። የራሳቸዉ የሆነ ዉስጣዊ ተግዳሮት ደግሞ አላቸዉ። ይህም በሚያስቡት መንገድ ሆነ፣ በሚናገሩትና በሚያደርጉት ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሲሞክሩ የሚፈታተናቸዉ ነዉ። ኃጢአታችን አንዳችን ከሌላዉ ጋር እንዳንኖር፣ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን እንዳንወድ ከባድ ያደርገዋል። ትክክል ነኝ? አንዳንድ ጊዜ ባሎቻችንንና ሚስቶቻችንን መዉደድ ከባድ ሊሆን ይችላል አይደለም እንዴ ? ኢየሱስ እንደዚሁም ጠላቶቻችን እንድንወድ ተናግሮናል። ወገኖቼ እነዚህ ነገሮች በርግጥ ለእኔ ከባድ ነገሮች ናቸዉ።

በዉስጣችን ያለዉን ጠላት ለማሸነፍ ጉልበት የለንም። እግዚአብሔርን ወይም በዙሪያችን ያሉትን ሰዎች መዉደድ እንደሚገባን ለመዉደድ በቂ ጉልበት የለንም። እኛ በምንፈልገዉ መንገድ ብቻ ነዉ። ከዚህም የተነሳ ነዉከእግዚአብሔር የሚመጣዉን ኃይል የመፈለጋችን ሚስጢር።

የጳዉሎስን የተለያዩ የፀሎት ተሞክሮች ለመረዳት የሚያግዘኝን ይህን ሥዕል ሠራሁ። ጳዉሎስ የፀለየበትን የተለያየ ነገሮች በምንመለከትበት ጊዜ ይህንን ስዕል ለማካፈል እሞክራለሁ። ይህም በመንፈሱ አማካኝነት በዉስጣችን ጥንካሬ የሚሰጠንን ኃይል ያካትታል።




### 17ሀ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት ይኖር ዘንድ ነዉ (ካቶኪዮ እንጂ ፓሪዮኮስ አይደለም)

ጳዉሎስ የፀለየበት ሁለተኛዉ ነገር ክርስቶስ በልባችን ዉስጥ እንዲኖርና እንዲያድግ ነዉ። በዚህ ቦታ የግሪኩ ቃል ካቶኪዎ የሚለዉ ነዉ። ፓሪዮኮስ ከሚለዉ የግሪኩ ቃል የተለየ ነዉ። ፓሪዮኮስ ጎብኝ፣ መፃተኛና ስደተኛ ማንንት ያለዉ ሰዉ ማለት ነዉ።

**ሐዋርያት ሥራ 7: 29**

29 ሙሴም ከዚህ ነገር የተነሳ ሸሽቶ በምድያም አገር መጻተኛ ሆኖ ኖረ።

ሙሴ በምድያም 40 ዓመት ኖረ፡፡ ነገር ግን በትክክል የርሱ ቤት አልነበረም። እርሱ ሁልጊዜ የዉጭ ሰዉ መጻተኛም ነበር። ዜጋም አልሆነም። አንዳንዶቻችሁ በዚያ ሁኔታ ዉስጥ ነዉ ያላችሁት አይደለም? እናንተ አሁን በአሜሪካ ዉስጥ ነዉ ያላችሁት። ነገር ግን ዜግነት የላችሁም። ፖስፖርታችሁ የፓኪስታን ነዉ ወይም የግብጽ ወይም የሌላ ሐገር። እናንተ ፓሪዮኮስ ናችሁ። የአሜሪካ ዜጋ ስትሆኑ ካቶኪዮ መሆናችሁን ለማረጋገጥ የአሜሪካን ፓስፖርት ታገኛላችሁ። የግሪኩ ቃል በአንድ ቦታ በቋሚነት የሚኖር ማለት ነዉ። ነዋሪ እንጂ ጎብኝ አይደለም

**ሐዋርያት ሥራ 9: 35**

35 በልዳና በሰሮናም የሚኖሩ(ካታኪዮ) ሁሉ እርሱን ተመልክተዉት ወደ ጌታ ዘወር አሉ

ጳዉሎስ ክርስቶስ በልባችን ዉስጥ ካታኪዮ እንዲሆን ይፀልያል። ይሄ የቱን ያህል አስደናቂ እንደሆነ ታያለህ? አንተ የኢየሱስ ተከታይ ከሆንክ እርሱ ጎብኝ አይደለም። መፃተኛም አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ ቋሚ ቤቱን በልብህና በልቤ ዉስጥ ያደርጋል።

ክርስቶስ በልብህ ለመኖር እንዴት ነዉ ወደአንተ መምጣት የሚችለዉ? ክርስቶስ በእምነት አማካኝኝነት በልብህ መኖር ይችል ዘንድ ጳዉሎስ ይፀልያል። ያ ምን ማለት ነዉ? እምነት በልብህ ዉስጥ ልክ እንደበር መሆኑ ነዉ። ኢየሱስ በዚያ በር በኩል መግባት ይኖርበታል። ነገር ግን በሩ ከተዘጋ ኢየሱስ በዉጭ ይቆያል። በዉስጥህ ሊኖርና ካታኪዮ ሊሆን አይመጣም።

ለአሥር ዓመት ያህል ለክርስቶስ የተዘጋ ልብ ነበረኝ። እርሱ እዉነተኛ እንደሆነ እምነት አልነበረኝም። በሌላ ነገሮች እምነት ነበረኝ። ጭፈራዎችና ልጃገረዶች ደስተኛ ሊያደርጉኝ እንደሚችሉ እምነት ነበረኝ። ጠንካራና ስኬታማ መሆን በልቤ ሠላምን ማምጣት እንደሚችሉ አምኜ ነበር።

ነገር ግን አይችሉም። ደስታ፣ ሠላምና ደህንነት ሊያመጡልህ የሚችሉት ነገሮች ምድናቸዉ? እባክህ ጓደኛየ እነዚህ ሁሉ እንደሚዋሹህ እወቅ። ለኃጢአትህ ያለህ መሰጠት፣ የምታመልካቸዉ ጣዖቶች የልብህን በር ዝግ ያደርጉታል። ከእግዚአብሔር ነፃ ሆነህ ለመኖር ያለህ ፍላጎት ለኢየሱስ የልብህን በር ዝግ ያደርጉታል። ለእግዚአብሔር "አንተ ብቸኛዉ እዉነተኛ አምላክ ነህ ኃጢአተኛ ልቤ ባንተ ላይ አመፀኛ ነዉ ማለት ስትጀምር ሁሉም ነገር ይቀየራል። ኃጢአቴ ልብህን ይጎዳል፣ ኃጢአቴ ነዉ ክርስቶስን ለመስቀል ሞት አሳልፎ የሰጠዉ። አባቴ ሆይ በኢየሱስ ስም ይቅር በለኝ ፈዉሰኝም።"

ልታደርግ የሚገባህ ያ ነዉ። ለልብህ በር ቁልፉ ንስሃና በኃጢአትህ ዙሪያ ያለህ ታማኝነት ነዉ። መንፈስ ቅዱስ ለማመን እምነትን ሊሰጥህ ዝግጁ ነዉ። ይኸዉም ኢየሱስ ኃጢአትህን ይቅር ማለት እንደሚችልና በልብህ ለዘላለም የመኖሩ ጉዳይ ነዉ።

ብዙዉን ጊዜየን ያጠፋሁት በቁጥር 17 ላይ ነዉ። ምክኒያቱም ጳዉሎስ ይፀልይበት የነበረዉ ነገር ኢየሱስ በዉስጥህ መኖር ካልቻለ በስተቀር ትክክል አይሆንም። ነገር ግን የሚኖር ከሆነ እግዚአብሔር ለአንተ ስላለዉ እነዚህ ተስፋዎች መደነቅ ትችላለህ። የሚቀጥለዉን እንመልከት፡

## 17ለ የእናንተ ሥራና መሠረት በፍቅር ይፀና ዘንድ ነዉ

ዛፍ ጠንካራ ሥሮች ከሌሉት በስተቀር በማዕበል መሃል ሊቆም አይችልም። ቤት በጽኑ መሠረት ላይ ካላረፈ በምድር መናወጥ ምክኒያት ሕልዉናዉ ሊቀጥል አይችልም። ሕይወታችንም እንደዚያዉ ነዉ። ለዚህ ነዉ መዝሙረኛዉ 1ሀ ምስጉን ነዉ .......3ሀ እርሱም በዉሃ ዳር እንደተተከለች ዛፍ ይሆናል የሚለዉ።

ጳዉሎስ ክርስቲያኖች በፍቅር ስር እንዲሰዱና መሠረት እንዲጥሉ ይፀልያል። ሥሮች ዉሃና አልሚ ምግቦችን ለማግኘት ወደምድር ሠርገዉ ይገባሉ። ወደላይ ለማደግ ኃይል፣ በማዕበል ለመጽናት ደግሞ ጥልቅ የሆነ ሥር ያስፈልጋቸዋል። እኔና እናንተም እንደዚያዉ። የእግዚአብሔርን ኃይል የምናገኘዉ በእርሱ ፍቅር ዉስጥ ሰምጦ በመገኘትና፡ ቃሉን በማንበብ፣ በየእሁዱ ቤተ ክርስቲያን በመሰብሰብ፣ የጌታን እራት በመካፈል፣ በየእለቱ ብቻችንንና ከሌሎች ጋር በመፀለይ ይሆናል። እኛም እንደዚያዉ።

## 18ሀ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ለማስተዋል እንበረታ ዘንድ

ጳዉሎስ የክርስቶን ፍቅርና ኃይል ለማስተዋል(ለማወቅ) ብርታት እንዲሆንልን ይፀልያል። ነገር ግን አስተዉሉ ይሄን የምናዉቀዉ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ነዉ። ይሄ በርግጥ በጣም ጠቃሚ ነዉ። ጳዉሎስ የእግዚአብሔርን ፍቅር በራሴ ብቻ በበቂ ሁኔታ ለማወቅ እንደማልችል ይናገረኛል። ከተወሰኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ከሆንክ የተወሰነዉን የቃሉን እዉነት ብቻ ነዉ መረዳት የሚቻልህ። እንዳንተ ካሉት ሕዝብ ጋር ሕብረት ካደረግህ ብቻ ነዉ። ጳዉሎስ እየፀለየበት ያለዉን በረከት ለመካፈል እርስ በራስ መፈላለግ ይኖርብናል። ስለእግዚአብሔር የበለጠ የማዉቀዉ ሁላችሁን ማወቅ ከቻልኩ ብቻ ነዉ። ምክኒያቱም በዚያ ዉስጥ የምናዉቀዉ እምቅ ነገር ይኖራል።

## 18ለ ስፋቱና ርዝመቱ፣ ከፍታዉና ጥልቀቱ ምንድነዉ

ግራዉ ከቀኙ የቱን ያህል ይርቃል? ከምስራቅ ወደምዕራብ ወይም ከሰሜን ወደደቡብ መለካት ትችላለህ ወይ? ጽንፈ ዓለማችን የቱን ያህል ትልቅ ነዉ? ለመለካት ያስቸግራል። እንሚመስለኝ ጳዉሎስ የክርስቶስን ፍቅር በተመለከተ በዚህ ቦታ እየተናገረ ያለዉ ይህንን ነዉ። እናም ከምናስበዉ

በላይ የሰፋና የረዘመ ነዉ። እግዚአብሔር ፍቅሩን አንድ ቋንቋ ለሚናገሩ ለአንድ ዓይነት ሕዝብ ብቻ አይገድብም። በታሪክ እግዚአብሔር በምድር ላይ ያሉትን ሕዝቦች ሁሉ ምንጊዜም ወደመንግስቱ የመጋበዝ እቅድ አለዉ።

የእግዚአብሔር ፍቅር እኛ ከምናስበዉ በላይ ከፍታና ጥልቀት አለዉ። በምድር ላይ ይቅር የማይባል ኃጢአተኛ የለም። የእግዚአብሔርን ሕግ በመቶዎች ለሚቆጠር ጊዜ መጣስ ትችላለህ፣ ንስሃ መግባትና ክርስቶስን ማመን እስከቻልክ ጊዜ ድረስ የክርስቶስ ደም ሊያነጻህና በየዋህነት ሊያኖርህ በቂ ነዉ። ይሄ እዉነት ለጎረቤቶቻችን በሙሉ የክርስቶስን ፍቅር ልንነግራቸዉ ድፍረትና ጥንካሬ ሊሰጠን ይገባል። ምክኒያቱም እነርሱም እንደእኛ እንዲሆኑ ስለምንፈልግ።

## 19ሀ ከመታወቅም የሚያልፈዉን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ

የክርስቶስ ፍቅር የሕይወታችን ሥርና መሠረት ነዉ። የክርስቶስ ፍቅር እርስ በርሳችን እንደዚሁ እንድንዋደድ ኃይል ይሰጠናል። በጨዋዎቹ ዓመታት ለሕዝብ ተደራሽ ለማድረግ በምንከፍትበት ጊዜ በቤተክርስቲያናችን ብዙ ጎብኝዎች እንዲኖሩን እንፀልያለን። በአንድነት ስንዘምር፣ ስንፀልይና ስናመልክ ይመለከቱናል። እርስ በርሳችን ስንፈቃቀር፣ ስንበራረክና ስንገላገል ሊያዩን ይገባል፡የክርስቶስ ፍቅር በእኛ ሲገለጽ ጣዕሙ ይረዳሉ። እኛ ከተለያየ ሃገርና ባሕል የተዉጣጣን ነን። በሰዎች መረዳት አንድ ቤተሰብ ልንሆን የሚቻል አይመስልም። ነገር ግን እዉነቱ እንደዚያ ነዉ አሁንም ጨምረን እንደቤተሰብ እናድጋለን ትክክል አይደለም? በሚስፈልገን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ሲሞላን እናድጋለን። የቁጥር 19ኝን ሁለተኛዉን ክፍል ተመልከቱ፡

## 19ለ እስከእግዚአብሔርም ፍፁም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ ነዉ።

በነዚህ ቁጥሮች ግሶችን ካየህ ሁሉን የሚያደርገዉ እግዚአብሔር እንደሆነ ታስተዉላለህ። አባት ያጠነክረናል። መንፈስ ኃይልን ይሰጠናል። ክርስቶስ በልባችን ይኖራል። መላዉ የሥላሴ አካል እኛን ለመባረክ በእኛ ላይ ሁሉን ነገር አድርገዋል። አባታችን በመንፈሱ በኩል በክርስቶስ ፍቅር እዉቀት ሞልቶናል።

ጳዉሎስ ራስህን በእግዚአብሔር ሙላ ማለቱ አይደለም። ጳዉሎስ በእግዚአብሔር ትሞላ ዘንድ እየፀለየ ነዉ ያለዉ። የእኛ ድርሻ ግልጽና ራሳችንን በማዘጋጀት የእግዚአብሔርን በረከት መቀበል ነዉ። ያንን እንዴት እናደርጋለን? በርግጥ እግዚአብሔር በዚህ ቦታ ለእኛ አንድ ነገር ሊያደርግ አለዉ ልክ አይደለም?

አንድ የምናደርገዉ ነገር ቢኖር ጳዉሎስ በነዚህ ቁጥሮች እንዳደረገዉ መፀለይ ነዉ። ቆይቶ በዚህ ደብዳቤ ለእግዚአብሔር ሥራ ራሳችንን ዝግጁ ከማድረግ አንፃር ማድረግ ያለብንን ነገር በተመለከተ አንዳንድ ምክሮች ይለግሰናል።

**ኤፌሶን 5: 18-21**

18 በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ ይህ ብክነት ነውና።

19 በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤

20 ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ።

21 ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ።

ይህም በዚህች ቤተ ክርስቲያን እንደወንድምና እህት ምን ማድረግ እንደሚገባን የተሰጠ መግለጫ ነዉ። ጓደኞቼ እርስ በርሳችን ልንበረታታ፣ ልንረዳዳና ልንደጋገፍ ይገባናል። በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር ሥራዉን በሕይወታችን በየግል በሚፈጽምበት ጊዜ እኛም እነዚህ ነገሮች እናከናዉናለን። ዉጤቱም ጠንካራ፣ ጤናማ የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ይሆናል። ያ ነዉ በሕብረት የምንፀልይበት ነገር።

## 3. ኃይል 3 – ለምን እንፀልያለን

ጳዉሎስ ዛሬ እንዳየነዉ አስደናቂ ነገር ሊያደርጉ ስለሚችሉት ብቻ ይፀልያል። "እዉቀትን ስለሚያልፈዉ" ብቸኛዉ ፍቅሩና "እንደክብሩ ባለጠግነት መጠን የሚሰጥ " ብቸኛ ማንነት ያለዉ ነዉ።" ጳዉሎስ ፀሎቱን የጨረሰዉ በቁጥር 20 ጀምሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ በጣም ዉብ በሆኑ ቃላት ነዉ……

## 20ሀ ከምንለምነዉ ወይም ከምናስበዉ ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለዉ

እኔና ባለቤቴ በየእለቱ የማለዳ ፀሎታችንን በአንድነት የምንጨርሰዉ በጥቅስ ቁጥር 20 እና 21 ነዉ። እነዚህ ቁጥሮች ፀሎትን በሚመልሰዉ አምላካችን ያለንን መታመን ይገልጻሉ። እንደዚሁም ወደኃይለኛዉ እግዚአብሔር የምንፀልይበትን ምክኒያት ያሳዩናል። ኃይሉ ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ ጳዉሎስ ያንን ለመግለጽ አንድ ቃል ብቻ መጠቀም አልቻለም። ጳዉሎስ እንዲህ ማለት ይችል ነበር፡

እግዚአብሔር ከምንጠይቀዉ በላይ ሊያደርግ ይቻለዋል።

ነገር ግን ያ በቂ አይደለም። አይደለም እንዴ? በእንግሊዘኛዉ ትርጉም እንዲህ የሚል አለን፡

እግዚአብሔር ከምጠይቀዉ በላይ የበዛ ነገር ሊያደር ይችላል።

እግዚአብሔር ከምንጠይቀዉ በላይ በጣም የተትረፈረፈ ነገር ሊያደርግ ይችላል።

እግዚአብሔር ከምንጠይቀዉ ነገር ሁሉ በላይ በጣም የበዛ ነገር ሊያደርግ ይችላል።

እግዚአብሔር ከምጠይቀዉ ነገር ወይም ከምናስበዉ ነገር ሁሉ በላይ በጣም የበዛ ነገር ሊያደርግ ይችላል።

ወገኖቼ ይሄ ፀሎታችንን የምናቀርብለት አምላክ መሆኑን ትገነዘባላችሁ? ለምንድነዉ መፀለያችንን የምንረሳዉ ወይም ለመፀለይ ችላ የምንለዉ? ስለሁሉም ነገር አብዝተን ለመፀለይ እርስ በራሳችን እንበረታታ። ምክያቱም በምንፀልይበት ጊዜ በቅርበት በሰማይ ሆኖ ከሚሰማን አባታችን ፍቅርና ኃይል የተነሳ ነዉ።

## 20ለ እንግዲህ በእኛ ዉስጥ ሆኖ እንደሚሠራዉ ኃይል መጠን ነዉ

ይሄ ወደቁጥር 15 ይመልሰናል ይኸዉም ጳዉሎስ እግዚአብሔር "በመንፈሱ አማካኝነት ትበረታቱ ኃይሉን ያስታጥቃችኋል።" መንፈስ ቅዱስ በዉስጣችን በኃይል ይሠራል። ያ ሥጋዊ ኃይል አይደለም። ያ ጳዉሎስ እየተናገረ ያለዉ የማወቅ፣ የመረዳትና ማንኛዉንም ነገር የማመን ኃይል ነዉ:ያ ነዉ በዉስጣችን ሊለዉጠን የቻለዉ። ከዚያም በዉጭ ያለዉ ባሕርያችንና ሕይወታችን መለወጥ ደግሞ ችለዋል። የተለወጠዉ ሕይወታችን ለእግዚአብሔር ክብር ያመጣል። ስለዚህም ነዉ ጳዉሎስ የሚፀልየዉ፡

## 21ሀ ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ክብር ይሁን ።

እንደግለሰብ በእኛ ዉስጥና እንደቤተክርስቲያን ከሚሠራዉ ነገር የተነሳ የእግዚአብሔር ክብርና ማንንት ለመላዉ ዓለም ታዉጇል ከፍ ከፍ ብሏል፡ ጳዉሎስ በቤተ ክርስቲያን ዉስጥ የክርስቶስ ኢየሱስ ክብር እንዲታይ ፀለየ። የአንድ ድምጽ ሕብረት ታዋቂ ቤተ ክርስቲያን እንድትሆን አንፀልይም። እኔም ታዋቂ መጋቢ ወይም ሰባኪ ለመሆን አልፀልይም። የራሳችንን ክብር መፈለግ የለብንም። በእነዚህ ተስፋዎች መሠረት እግዚአብሔር ብቻ ነዉ ክብር የሚገባዉና ሊቀበል የሚገባዉ። ምክያቱም፡

"መለኮታዊ ኃይል ብቻ በመለኮታዊ ማህበረሰብ ዉስጥ መለኮታዊ ፍቅር ማፍራት ይችላል።" (ጆን እስቶት)

## 21ለ እስከትዉልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከዘለዓለም ክብር ይሁን አሜን።

ሁሉም ትዉልድ በታሪክ እግዚአብሔር ከእኛ በፊት ለኖሩት ወንዶችና ሴቶች ያለዉን ታማኝነት ወደኋላ ተመልሶ ይመለከታል። ዘለዓለም የወደፊቱን ይመለከታል። በሰማይ ያለዉን መልካሙን አባታችንን የልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን አባት እንዲሆን ማመን እንችላለን። ይህችን ቤተ ክርስቲያን እንዲያሳድግ፣ ለዚህ ዓመትና ለሚመጡትም ዓመታት የሚስፈልገንን እንዲሰጠን እናምነዋለን።

የጳዉሎስ ፀሎት የመጨረሻዉ ቃል አሜን ነዉ። ምናልባት በእናንተ ዘንድ እንደሚታወቀዉ አሜን ማለት እዉነት ነዉ ወይም እስማማለሁ ማለት ነዉ። ኢየሱስ ይኸንን

**ዮሐንስ 5: 24**

24 ላይ እዉነት እዉነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለዉ፣ ከሞትም ወደሕይወት ተሸገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።

በእብራይስጡ ቋንቋ ኢየሱስ አረፍተ ነገሩን በአሜን አሜን ነዉ የጀመረዉ። ለዚህም ምክኒያቱ የሚለዉ ነገር እዉነት እንደሆነ እንዲያዉቁ ነዉ። እዉነት በመሆኑም ከጳዉሎስ ፀሎት የምንማረዉ ነገር ይሄንን ፀሎት የራስችን ማድረግን ነዉ። እንደዚሁም የእዉነት አምላክ በምንፀልይበት ጊዜ እንደሚሰማን በርሱ መታመንን ነዉ።

## አሁን ወደዚህ የፍቅርና የኃይል አምላክ በአንድነት እንፀልይ፡

ጌታ ኢየሱስ ሆይ ታስፈልገናለህ። በልባችን እንድትኖርና ዉስጣችንን እንድትቀይር እንፈልግሃለን። በዉስጣችን ያለዉን ኃጢአት እንድታነጻ በፍቅርና በሠላም እንድትተካዉ እንፈልጋለን። ሰማያዊ አባታችን ሆይ በሕይወታችን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ለኃጢአት የለም ማለት እንደንችል ኃይልን ስጠን። ኢየሱስ እንደወደደን እርስ በርሳችን እንድንዋደድ እርዳን። ይህንን ነገር በዉስጣችን ስታከናዉን በእኛ ዓይንና በዓለም ዘንድ ትከብራለህ። እንደተለወጡ ሰዎች እርስ በርሳችን መስዋዕትነት በተሞላዉ ሁኔታ እንገላገላለን እንዋደዳለንም። ከዚህም የተነሳ በኢየሱስ ስም አማካኝነት ኃይል እንዳለ ዓለም ሁሉ ያዉቃል። በስሙ እንፀልያለን። አሜን!!